ECODE
ETHIOPIAN CODERS INITIATIVE

# በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የምስራቅ ጉራጌ ዞን 15,572 ኮደሮች ኢንሼቲቭ

## የስትሪንግ ኮሚቴ ማስፈጸሚያ ዕቅድ




ነሐሴ / 2016
ቡታጅራ

# መግቢያ

በዓለም አቀፍ ደረጃ የዲጂታል ክህሎት በዲጂታል የታገዘ ማህበረሰብ ለመፍጠር፣ አዳዲስ የስራ እድሎችን ለመፍጠር እና በነሱም ላይ ለመሰማራት ወሳኝ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል፤ ነገር ግን ሀገራችና ክልላችን ብሎም ዞናችን በአሁኑ ወቅት በተመሳሳይ እድገት ደረጃ ጋር ካሉ አገራት ጭምር በዲጂታል ክህሎት ወደ ኃላ ቀርታለች። የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ በርካታ ወጣቶችን የሚያሳትፉ የዲጂታል ክህሎት ፕሮግራሞች ለአገራችን ስትራቴጂያዊ ጥቅም አላቸው ብሎ ያስቀምጣል። አዲሱ ትውልድ ተገቢው የዲጂታል ክህሎት ከሌለው በአለም አቀፍ ደረጃ ለራሱም ተወዳዳሪ አይሆንም እንደ አገርም ፣እንደ ክልላችንም፣ እንደ ዞናችንም ተወዳዳሪነታችንን ይጎዳል።

# … የቀጠለ

ስለሆነም እንደ ዞናችን በዲጂታል ክህሎት ያለብንን ክፍተት ለመሙላት የመሰረታዊ የኮምፒውተር እውቀት እና ሁለንተናዊ የዲጂታል ክህሎት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ለክልላችን ወጣቶች ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል። እንደ ሀገር የ "5 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ኮደርስ" ፕሮግራም አካል የሆነውን ስልጠና እንደ ክልላችን ለ198,284 ኮደርስ ፣ እንደ ዞናችን ለ 15,572 ኮደርስ በማመቻቸት ወጣቶች ተገቢው የዲጂታል ክህሎት እንዲኖራቸው ለማድግ የተቀረጸ ፕሮግራም ሲሆን የዚህ ፕሮግራም ስትሪንግ ኮሚቴ ማስፈጸምያ እቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

# ኢትዮጵያ ኮደርስ ፕሮግራም ምንነት እና አላማ

የዲጂታል ክህሎት ስልጠና መርሃ ግብር ነው።

ወጣቱ ትውልድ በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ መሳተፍ የሚያስችለውን የዲጂታል ክህሎት እንዲኖረው ማስቻል ነው።

እ.ኤ.አ በ2026 **198,284** የክልላችንን ወጣቶችን የዲጂታል ክህሎትን ማስታጠቅን ግብ ያደረገ ነው

ለዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂ ትግበራ ስኬት እና ተወዳዳሪነት ከፍተኛ አስተዋጽዎ ይኖረዋል ።

ECODE
ETHIOPIAN CODERS INITIATIVE

# 15,572 ምስራቅ ጉራጌ ዞን ኮደርስ ፕሮግራም ሰጭ አካላት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

الإمارات العربية المتحدة

UDACITY

**Misraq Gurage Zone coders coders**



# የስልጠና ርዕሶች/ https://ethiocoders.et/

### ANDROID KOTLIN DEVELOPMENT FUNDAMENTALS

This track aims to teach you the core fundamentals of Android development

### PROGRAMMING FUNDAMENTALS

This track aims to teach you the core fundamentals of web development

### DATA SCIENCE FUNDAMENTALS

This track aims to teach you the core fundamentals of Data Analysis

## የስልጠናው ግብ

- በሚቀጥሉት 3 ዓመታት በቁጥር 15,572 የዞናችንን ወጣቶችን በፕሮግራሚንግ፣ በዳታ ሳይንስ፣ አንድሮይድ እና በሌሎችም ዘርፎች የዲጂታል ሊትሬስ ክህሎት ባለቤት ሆኗል፡፡
- በዞን፣ በክልል፣ በሀገር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በቴክኖሎጂ ብቁና ተወዳደሪ የሆነ የፈጠራ ችሎታና ክህሎት ያለው ወጣት ማፍራት ተችሏል፡፡

## የስልጠናው ተሳታፊዎችን በተመለከተ

በክልላችን ለሁሉም አካባቢዎች ተደራሽና አሳታፊ መሆን አለበት፡፡

- ከ11ኛ ክፍል ጀምሮ ፈላጎት ያለቸው የክልላችን ዜጎች ልሳታፉ ይችላሉ፤
- በትምህርት ላይ ያሉ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣
- በመንግስት ሥራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች፣
- ለዲጂታል ቴክኖሎጂ ቅርበትና ፍላጎት ያላቸው አካላት፤
- አንድ ሰው አንድ ስልጠና ላይ ብቻ ነው መሳታፊ የሚችለው፣

## የስልጠናው ትግበራው ሂደት

- ሰልጣኞች በፕላትፎርሙ በመመዝገብ ኮርሶቹን ኦንላይን በመውሰድ የዲጂታል ሊትሬሲ ቴክኖሎጂ ቴክኒካል ክህሎትን የሚያሳድጉ ይሆናል።
- አንዱ ኮርስ እስከ 6 ሳምንት ሊወስድ ይችላል። በኦንላይን ለየኮርሶቹ አማካሪዎች እና ውይይት የሚያደርግ የኦንላይን ኮሚኒቲ ይኖራል።
- ኮርሱን በአግባቡ ተከታትሎ የጨረሰና የማጠቃለያ ፈተና ያለፈ ሰልጣኝ አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሰርተፊኬት ከካምፓኒው ይሰጣል።
- እንዲሁም ከስልጠና በኃላ የሚሰጠውን ፈተና ተፈትኖ ጥሩ ውጤት ለስመዘገቡ ሠልጣኞች ብቻ ቀጣይ አድቫንስድ ስልጠና እንድወስዱ በማበረታቻ መልክ የሚሳጥ ይሆናል፡፡

# … የቀጠለ

የፕሮግራሙን ተግባራዊነት በዋናነት በዞናችን ባለድርሻ አካላት እና በወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች ተሳትፎ የሚፈጸም ይሆናል። የባለድርሻ አካላት እና የወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የስራ ድርሻ እና የሰልጣኝ ብዛት ከታች የተዘረዘረ ሲሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት እና ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የተሰጣቸውን የስራ ዝርዝር መሰረት ያደረገ የድርጊት መርሃ ግብር እንደየ ስራ ዝርዝራቸው በፍጥነት አዘጋጅተው ለቴክኒክ ኮሚቴው ያቀርባሉ።

## የስልጠና ማዕከላት

በዞናችንን የሚገኙ የተለያዩ የመንግስት እና የግል ተቋማት ለዚሁ ስልጠና የሚሆን የብሮድባንድ ኢንተርኔትና የኮምፒዩተር ላብራቶሪዎች ዝግጅት እንድያደርጉ በመስተባባር መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በዚሁ መሠረት ስልጠናው በዋናነት በዞናችን ባሉት የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች፣ የግል ኮሌጆች፤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና ሌሎችንም ለስልጠናው አመቺ በሆኑ ቦታዎች የምሰጥ ይሆናል፡፡

## መነሻ ሁኔታ /ጥንካሬዎች/Strength

- በዞናችን በሁሉም አከባቢዎች ስልጠናውን ተደራሽ ለማድረግ የኢኮቴ መሠረተ ልማት እና የኔትወርክ ሽፈን ተደራሽነት ያለ መሆኑ፣
- በዞናችን ደረጃ ወጣቶችን በዲጂታል ቴክኖሎጂ ቴክኒካል ክህሎት ለመጎልበት ከፍተኛ ፊላጎት ያለ መሆኑ፣
- ት/ት ቤቶችን፤ ኮሌጆችንና ሌሎችንም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን አስተባብሮ መጠቀም የሚቻል መሆኑ፤
- ስልጠናውን በተገቢ ሁኔታ ለማስኬድ በሁሉም አከባቢዎች በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም የስልጠና ማዕከላት ያለ መሆኑ፣
- ስልጠናው በይነ-መረብ የምሰጥ በመሆኑ ሁሉም ሰልጠኝ መደበኛ አገልግሎቶችን ለተገልጋይ እየሰጠ ባለበት አካባቢ ሆኖ የሚወስድ ስልጠና መሆኑ፤

# ስልጠና የሚጀምርበት መርሀ-ግብር

በፌዴራል ደረጃ በሀምሌ 16/2016 ዓ.ም ለማስጀመር ዕቅድ የተያዘ ሲሆን በማዕካላዊ ኢትዮጵያ ክልል ደረጃ የፌዴራል በመርሀ-ግብሩ በተጀመረ ማግስት ክልላዊ ተደርጎ ሲሆን በዞናችን ደግሞ የክልል በመርሀ-ግብሩ በተጀመረ ማግስት የሚጀመር ይሆናል፡፡

## ድክመቶች/weakness

- የግብአት አቅርቦት እጥረት፤
- ስልጠናው በሚካሄድበት ጊዜ መብራት መጥፋትና ስልጠናው በተጠበቀው ጊዜ እንዳይካሄድ መስተጓጉል ልፈጠር ይችላል፣
- ፕሮግራሙን ለሚያስተባብሩ አካላት በቂና ተመጣጣኝ ሁኔታ ያለማመቻቸት፤
- የስልጠና ሰዓት አጠቃቀም ክፍተት ልኖር ይችላል፣

## መልካም አጋጣሚዎች /Opportunities እንደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ

- በዞናችን የሚገኙ የመንግስት ተቋማት፣ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች በአጠቃላይ ማህበረሰባችን ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ከማስፋፋትና ከመጠቀም አንጻር ፍላጎታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ፤
- ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ከማስፋፋት አንጻር የተቋማት ፍላጎት እያደገ መምጣቱ፤
- በክልል፣ በዞን እንዲሁም እስከ ወረዳና ከተማ አስተዳደር ድረስ የዲጂታል ኮደር ፕሮግራምን ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀትና የሰዉ ሃይል መኖሩ፤
- በዞንችን በሁሉም አከባቢ ስልጠናውን ለማስኬድ የሚያስችል የኢኮቴ መሠረተ ልማትና የኔትወርክ ሽፈን ተደራሽ መሆኑ፤

# ስጋቶች /Threats

- በክልል፣ በዞኖች፣ በልዩ ወረዳ የኮደር ፕሮገራም ለሚያስተባብሩ አማካሪዎች፣ ኮሚቴዎች እና ሌሎች አስተባባሪ ባለድርሻ አካለት ለታቀደው ስልጠና በቂ በጀት ከመንግስት ላይመደብ ይችላል፣
- ስልጠናውን በተሟላ መልኩ ለማስኬድ የስልጠና ማዕከላት ላይ ኢንተርኔት ብሮድባንድ መቆራረጥ፣ የኢንተርኔት ባንድዊድዝ አቅም አነስተኛ መሆን እና ኔትወርክ ብልሽት ወቅት ለጥገና ቶሎ ምላሽ ያለመስጠት ልያጋጥም ይችላል፤
- ለተማሪዎች ከመደበኛ ትምህርት ጋር መደራራብ ልያገጥም ይችላል፤
- የተወሰኑ ሰልጣኞች ስልጠናውን ጀምራው ልያቆርጡ ይችላሉ፤
- በትክክል ያልሰለጠኑ ሠልጣኞች የመጨረሻ ፈተና ላያልፉ ይችላሉ፤
- በአንላይን ምዝገባ ሂደት ላይ ክልላችንን በማይገልጽ ሁኔታ ሠልጠኞች ሊመዘገቡ ይችላሉ፤

# ክልላዊ ስትሪንግ ኮሚቴ

ክልላዊ ስትሪንግ ኮሚቴ በክልላችን ም/ር/መስተዳደር የሚመራ ሆኖ ዋና ሃላፊነቶቹም፡-

- ስለ ፕሮግራሙ በፌደራል ስትሪንግ ኮሚቴ የሚቀመጠውን አቅጣጫ ተከትሎ መፈጸምና ማስፈጸም፤
- ለፕሮግራሙ ተፈጻሚነት ክትትል እና ስልታዊ አቅጣጫ መስጠት፤
- የፕሮግራሙ አሰራር ስርዓት መዘርጋት እና መመሪያዎችን ማጽደቅ፤
- የፕሮግራሙን ሂደት መከታተል እና መገምገም፤
- ተግዳሮቶችን መፍታት እና አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ማድረግ፤
- ፕሮግራሙ በቀጣይ በሚሰፋበት ሁኔታ ላይ ውሳኔ መስጠት ናቸው።

# የኮሚቴው አባልነት

ECODES

- የትምህርት ቢሮ
- የር/መስተዳደር ጽ/ቤት
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ
- የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ
- የፕላን እና ልማት ቢሮ
- የፐብልክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ
- ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ
- የወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት
- የሴቶች ሊግ ጽ/ቤት
- ኢትዮ ቴሌኮም ደቡብ ደቡብ ሪጂን
- በክልላችን የሚገኙ 3ቱም ዩኒቨርሲቲዎች

## በዞኖችና ልዩ ወረዳዎች  ደረጃ የሚዋቀሩ አደረጃጀቶች

በዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ደረጃ የሚዋቀሩ ኮሚቴዎች፤ በክልል ደረጃ የተዋቀሩ ተመሳሳይ ኮሚቴዎችን ሆነው ተግባር እና ሃላፊነት  በየዞኖቹና ልዩ ወረዳዎቹ የሚተገብሩ ይሆናል።

# የሰልጣኞች ብዛት በየመዋቅሮች

| ተ.ቁ | መዋቅር | አንደኛ አመት | ሁለተኛ አመት | ሶስተኛ አመት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀዲያ | 14318 | 20045 | 22908 | 57271 |
| 2 | ስልጤ | 8995 | 12592 | 14391 | 35978 |
| 3 | ጉራጌ | 9376 | 13126 | 15001 | 37503 |
| 4 | ከምባታ | 6712 | 9397 | 10739 | 26848 |
| 5 | ሀላባ | 2846 | 3984 | 4552 | 11382 |
| 6 | ም/ጉራጌ | 3893 | 5450 | 6229 | 15572 |
| 7 | የም | 914 | 1279 | 1462 | 3655 |
| 8 | ጠምባሮ | 1187 | 1662 | 1898 | 4747 |
| 9 | ማረቆ | 734 | 1027 | 1173 | 2934 |
| 10 | ቀቤና | 574 | 803 | 917 | 2294 |
| 11 | ክልል ማዕከል | 15 | 20 | 23 | 58 |
| 12 | ድምር | | | | 198,284 |

# አመሰግናለሁ!!

በምስራቅ ጉራጌ ዞን
15,572 ኮደሮች
ኢንሼቲቭ

